# 9ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በሎስአንጀለስና በሲያትል ከተሞች በድምቀት ተከበረ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት የፀደቀበትን 20ኛ ዓመትና የ9ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል በደማቅ ሁኔታ በሎስአንጀለስና በሲያትል ከተሞች ታህሳስ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ተከበሮ ውሏል፡፡



ከተሳታፊዎች መካከል በከፊል

በሎስአንጀለስ ከተማ በዓሉ በተከበረበት ወቅት ወደ **400** የሚሆኑ የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ተወላጆች የተገኙ ሲሆን፣ የሀገራችን የተለያዩ ብሔር ብሔሰቦችና ህዝቦች አልባሳት፣ ምግቦችና መጠጦች እንዲሁም ባህላዊ ቁሳቁሶች ለተሳታፊዎች ለእይታ ቀርበዋል፡፡




በሎስ አንጀለስ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ቆ/ጀ/ጽ/ቤት ቆንስል ጄነራል የሆኑት ክቡር አምባሳደር ዘሪሁን ረታ በዓሉን አስመልክቶ ባደረጉት ንግግር በዓሉ «በህገ-መንግስታችን የደመቀው ኢትዮጵያዊነታችን ለህዳሴያችን» በሚል መሪ ቃል እየተከበረ መሆኑን በማውሳት፣

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለዘመናት ከተንሰራፋውና ስር ከሰደደው የእኩልነት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ረገጣና ጭቆና አገዛዝ ተላቀው ራሳቸው ወደውና ፈቅደው ባረቀቁትና ባፀደቁት ሕገ-መንግሥትና መርጠው በገነቡት ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሥርዓት መተዳደር ከጀመሩ እነሆ 20 ዓመታት እንደተቆጠሩ፤ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዴሞክራሲያዊ አግባብ የመመረጥና የመምረጥ እድል እንደተጎናጸፉ፤ በአገራዊ ጉዳይ ላይ በቀጥታም ይሁን በወኪሎቻቸው እኩል የመሳተፍና የመወሰን ዕድል እንዳገኙ፤ ራስን በራስ ከማስተዳደር አንስቶ ቋንቋቸውን ባህሎቻቸውንና ታሪኮቻቸውን ያለምንም መሸማቀቅ ማሳድግና መንከባከብ እንደቻሉ፤ የሃይማኖት እኩልነትን በተመለከተም ዜጐች በግልም ይሁን በጋራ የመረጡትን ሃይማኖት የማምለክ፣ የማስፋፋትና የማስተማር መብት የተደነገገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡




ክቡር አምባሳደር ዘሪሁን ረታታ ንግግር ሲያደርጉ

የዘንድሮው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል የሚከበረው የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን መጠናቀቂያ ላይ በመሆን የተመዘገቡ አመርቂ ውጤቶችን በማጣጣም በቀጣይ ደግሞ የሚጠብቀንን ከፍተኛ ስራ በማሰብ ራሳችንን በማዘጋጀት መሆን እንደሚገባ፤ በአገራችን እየታየ ያለው እድገት ሁሉንም የአገራችንን ዜጎችና የአገራችንን አካባቢዎች ያማከለ መሆኑን፤ በአገራችን የተመዘገበው እድገት ሰፊውን የህብረተሰብ ክፍል መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከተገኘው እድገት ሁሉም በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን እንዳስቻለ አስታውቀዋል።



የሎስአንጀለስ  የህዳሴ ምክር ቤት ሠብሳቢ የሆኑት አቶ ጃርሶ ደስታ በዓሉን በማስመልከት ባደረጉት ንግግር በሀገራችን የብሄር ብሔረሰቦች መብት የተከበረባት እና በህዝቦችም መካከል በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ አንድነት የተፈጠረ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ምክር ቤቱም በአገራችን የተጀመረውን የህዳሴ እንቅስቃሴ በሁሉም መስክ የተሳካ እንዲሆን ድጋፋቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገለፀዋል፡፡



በሎስአንጀለስ የህዳሴ ም/ቤት ስራ አስፈጻሚ አባላት

በመቀጠል ተሳታፊዎች የተለያዩ ይዘዋቸው የመጡትን ባህላዊ ምግቦች ለታዳሚዎች መስተንግዶ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ ተሳታፊዎችም የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ምግብና መጠጦችን በእንደዚህ አይነት ሁኔታ በአንድ ላይ ቀርቦ በማየታቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል፡፡ ተሳታፊዎች የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች እና ባህላዊ ውዝዋዜዎችና ጭፈራዎች አቅርበዋል፡፡



ወ/ሮ መብራት በየነ ፕሮግራሙን ሲመሩ

በተለያዩ የብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋዎችም ከተሳታፊዎች የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ተላልፏል። በበዓሉ መከበር የተሰማቸውንም ደስታ ገልጸዋል። በማስከተልም የእለቱ ፕሮግራም መሪ የቆ/ጄ/ጽ/ቤቱ ምክትል ቆንስል ጄኔራል የሆኑት ወ/ሮ መብራት በየነ በኩል ለተሳታፊዎች እለቱን በማስመልከት የተለያዩ የጥያቄና መልስ ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፣ ለተሳታፊዎችም ሽልማት ተሰጥቷል። በመቀጠልም ዲያስፖራው በሀገራችን እየተካሄደ ባለው የቤቶች ልማት ኘሮግራም ለመሳተፍ የሚያስፈልገው ቅድመ ዝግጅት፣ የዲያስፖራ አካውንት አከፋፈት፣ ዜግነታቸውን ለቀየሩ የትውልድ ኢትዮጵያ መታወቂያ አስፈላጊነት እና በህጋዊ መንገድ ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ስለመላክ አጭር መረጃ ለታሳታፊዎች ተሰጥቷል። በመጨረሻም በበዓሉ ላይ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ባህላዊ ዘፈኖች ቀርበው የዕለቱ ዝግጅት ተጠናቋል።

በተመሳሳይ መልኩ  በሲያትልና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን 9ኛውን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን ቀን ሲያትል በሚገኘው የኢትዮጵያና ሶማሌ ኮሚኒቲ እእና የትግራይ ኮሚኒቲ አስተባባሪነት ታህሳስ 12 ቀን 2007 ዓ.ም በደማቅ ሁኔታታ ተከብሩዋል። በበዓሉም ላይ ከ250 በላይ ታዳሚዎች ተገኝተዋል።

ከኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ካውንስል እና ከሶማሌ ኮሚኒቲ ተወካይና የዝግጅቱ አስተባባሪ የሆኑት አቶ መሀመድ ባደረጉት ንግግር የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ትልቅ ትርጉም እንዳለው፣ የህገመንግስቱ መጽደቅ የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ያጎናፀፍዋቸውን መብት በመጠቀም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ከመቼውም ግዜ የበለጠ ወዳጅነታቸው ጠንክሮ የልማት ተጠቃሚ እየሆኑ እንደመጡ ገልጸዋል።

በበዓሉ ላይ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች አባላት ተሳታፉ ሆነዋል፡፡ የበዓሉ ተሳፊዎችም በዓሉን በማስመልከት የተሰማቸውን ደስታና አስተያየት የገለጹ ሲሆን በዝግጅቱ ላይ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ባህላዊ ዘፈኖች ቀርበው የዕለቱ ዝግጅት በደማቅ ሁኔታታ ተጠናቋል፡፡